ኢ ሀ ሥ አ

# የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

ግንቦት ፡ 17 ፡ ቀን ፥ 1985 ፡ ዓ.ም. ።

## ዐጪር ፡ ማስታወሻ ፤ ትናንት ፡ ስለተነጋገርነው ፡ የመሳው ፡ ዐማራ ፡ ሕዝብ ፡ ሥያሜ ።

---

*[ግንቦት ፡ 17 ፡ ቀን ፡ 1985 ፡ ዓ.ም. ፥ የኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ ጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፥ ሊ.. ፡ ዤኔራል ፡ ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፥ ለቀድሞ ፡ መ.ዐ.ሕ.ድ. ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፡ ለፕሮፌሰር ፡ ዓሥራት ፡ ወልደየስ ፡ የጻፉላቸው ፡ ቈይታዊ ፡ ማስታወሻ ። የማስታወሻው ፡ የ 25 ፡ ዓመት ፡ የቈይታዊነት ፡ ዘመን ፡ በማክተሙና ፡ ለወቅቱም ፡ ተፈላጊ ፡ ሰነድ ፡ በመኾኑ ፥ ለመዠመሪያ ፡ ጊዜ ፡ ለሕዝብ ፡ ንባብ ፡ አቅርበነዋል ። ]*

---

*"ዐምሐራ"* ፡ ማለት ፤ *"ዐም"* ፡ ሕዝብ ፥ *"ሐራ"* ፡ ነጻ ፥ በተገናኝ ፡ *"ነጻ ፡ ሕዝብ"* ፡ ማለት ፡ ነው ። አመጣጡም ፥ ብዙው ፡ አፈ ፡ ታሪክ ፡ እንደሚያወጋውና ፡ እንዳንድ ፡ ጽሑፍ ፡ ታሪክ ፡ እንደሚያወሣው ፥ ከጌታችን ፡ ኢየሱስ ፡ ክርስቶስ ፡ ልደት ፡ ሺሕ ፡ ፱፻ ፡ ዓመት ፡ በፊት ፥ ዐሥራ ፡ ስምንቱ ፡ አንጋደ ፡ ሴም ፡ ከደቡብ ፡ ዐረብ ፡ ፈልሰው ፥ ነገደ ፡ ሕምያር ፣ ነገደ ፡ ዮቅጣን ፣ ነገደ ፡ ሐበሻት ፡ እያሠኙ ፥ ሀገረ ፡ ኵሽ ፡ (ኢትዮጵያ) ፡ ሲገቡ ፥ *"አንዳችን ፡ ካንዳችን ፡ እኩል ፡ ሐራ ፣ እኩል ፡ እግዚእ ፣ እኩል ፡ ማኅበር ፡ (ሕዝብ)"* ፡ ነን ፡ ብለው ፡ ራሳቸውን ፡ ያሳወቁበትና ፡ ያስጠሩበት ፡ የኹነት ፡ ስም ፡ ወይም ፡ የግብር ፡ ቅጽል ፡ ነው ፡ ሲሉ ፤ አንዳንዶቹም ፡ ከራሱ ፡ ከሕምያር ፡ የወረደ ፡ ቃል ፡ ነው ፡ ይላሉ ። ሌሎች ፡ ደግሞ ፥ አቤቶ ፡ ምንይልክ ፥ አባቱን ፡ ንጉሥ ፡ ሰሎሞንን ፡ ለማየትና ፡ ጥበቡን ፡ ለመቅሠም ፥ ኢየሩሳሌም ፡ ወርዶ ፥ ንጉሠ ፡ ጽዮን ፡ ተብሎ ፡ ሲመለስ ፥ ጽላተ ፡ ሙሴንና ፡ አብኳረ ፡ እስራኤላውያንን ፡ አስከትሎ ፡ ቢመጣ ፥ የሕዝብን ፡ መብት ፡ የምትጠነቅቅ ፡ ንግሥት ፡ ማክዳ ፡ በደስታ ፡ ተቀብላ ፥ እያንዳንዳቸውን ፡ የዕርሻ ፡ ምድር ፣ የመኖሪያ ፡ ቦታና ፡ የመቃብር ፡ መሬት ፡ በመትከል ፥ ባንድ ፡ ወገን ፡ በጭቃ ፡ ልደት ፤ በሌላው ፡ ወገን ፡ ደግሞ ፥ በምንይልክ ፡ ወላጅነት ፡ በመቀበል ፥ በሥጋ ፡ ልደት ፥ ከአበሻና ፡ ሐበሻት ፡ ጋራ ፡ አስተካክላ ፡ በአገሬነት ፡ ሠራቻቸው ። በእኩል ፡ እግዚእነትና ፡ በእኩል ፡ ዜጋነት ፡ አቁማ ፥ በኖረው ፡ የተወላጅ ፡ መብት ፥ የወል ፡ ልጃቸውን ፡ ዐብረዋት ፡ ያነግሡ ፡ ዘንድ ፥ ባንድ ፡ ሐራ ፡ ሠየምት ፡ ሕዝብነት ፡ አዋሐደቻቸው ። ዐብረዋትም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ ታሪክ ፡ የመዠመሪያውን ፡ ***ንጉሠ ፡ ነገሥት*** ፡ ቀዳማዊ ፡ ምንይልክን ፡ አነገሡ ። ከዚያ ፡ ጊዜም ፡ አንሥቶ ፥ ዐምሐራ ፥ ያንጋሹ ፣ የቀዳሹ ፣ የነጋሹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መሳው ፡ ሕዝብ ፡ የኹነትም ፡ የግብርም ፡ ስም ፡ ኾኖ ፡ ኖረ ፡ ይላል ። ሺሐብ ፡ ኧዲን ፡ ዐብደል ፡ ቀድር ፡ የተባለው ፡ የአሕመድ ፡ ግራኝ ፡ ታሪክ ፡ ጸሓፊ ፡— *"ቤተ ፡ ዐምሐራ ፡ ንጉሥ ፡ አንጋሾች ፡ ናቸው ፤ በነርሱ ፡ ያልተሠየመ ፡ ከቶ በኢትዮጵያ ፡ አይነግሥም ፤ ዐምሐራ ፡ ሠየምት ፡ ናቸው"* ፡ ብሎ ፡ በንግሥት ፡ ማክዳ ፡ ጊዜ ፡ የተፈጸመውን ፡ ታሪክ ፡ ይደግፋል ። ሌላም ፡ ሌላም ፡ የሚያክሉበት ፡ አይጠፉም ።

በማንኛውም ፡ በኩል ፥ ዐምሐራ ፡ ወይም ፡ ዐማራ ፥ ከጥንት ፡ ከመሠረት ፡ አንሥቶ ፡ የኵሽና ፡

ኢ ሀ ሥ አ

የሴም ፡ ተዋሕዶ ፡ ኾኖ ፡ የኖረው ፡ ያንጋሹ ፡ የኢትዮጵያ ፡ መላው ፡ ሕዝብ ፡ የወል ፡ የኹነት ፡ ወይም ፡ የግብር ፡ ስም ፡ እንጂ ፡ የዘር ፡ አይደለም ። ይህም ፡ በመኾኑ ፥ ዐማራ ፡ ከኢትዮጵያ ፡ ነገዶች ፡ ያንዱ ፡ ወይም ፡ የጥቂቶቹ ፡ ስም ፡ ነው ፡ ለማሠኘት ፡ አያስችልም ። ኹሉም ፡ ከኹሽና ፡ ከሴም ፡ ውሕደት ፡ የተወለዱ ፡ ስለ ፡ ኾኑ ፥ የኹሉም ፡ ነው ።

ዐማራ ፥ ስሙ ፡ እንደሚናገረው ፥ ባሕርይነቱ ፡ የወል ፡ እንጂ ፡ የግል ፡ አይደለም ። ይህም ፡ በመኾኑ ፥ ማንኛውም ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ነጻነቱ ፡ በኹሉ ፡ እንዲታወቅለትና ፡ እንዲከበርለት ፡ የሚወደውን ፡ ያኽል ፥ የሌሎችን ፡ ብጤዎቹን ፡ ነጻነት ፡ ያውቃል ፥ ያከብራልም ። ከዚህም ፡ የተነሣ ፥ ኹሉንም ፡ እኩል ፡ ይቀርባል ፥ ያቀርባል ። ከኹሉም ፡ በእኩል ፡ ፈንታ ፡ በመንፈስም ፡ በሥጋም ፡ ይቀላቀላል ። የብጤው ፡ ድኅነት ፡ ድኅነቱ ፥ ሞቱም ፡ ሞቱ ፡ ይኾናሉ ። በዚህ ፡ ብጤውን ፡ የማክበር ፡ ቸር ፡ ሞያው ፡ ነው ፥ እያንዳንዱ ፡ ኢትዮጵያዊ ፥ ርሱ ፡ ኹሉን ፡ ኾኖ ፥ ኹሉን ፡ ርሱን ፡ የሚያደርጋቸውና ፥ የኢትዮጵያ ፡ ነገዶች ፡ ኹሉ ፡ ባንድ ፡ ሐራ ፤ አገርን ፡ ሠሪ ፤ ንጉሥን ፡ ሿሚ ፡ ሻሪ ፡ ሕዝብነት ፡ ተዋሕደው ፡ የሚኖሩት ፤ ጠላት ፡ በየትኛውም ፡ ማእዘን ፡ በመጣም ፡ ቍጥር ፥ አንዳቸው ፡ ካንዳቸው ፡ ቀድሞ ፡ ለመሰለፍ ፡ እኩል ፡ የሚሯሯጡትና ፡ የሚጋደሉት ። ይኸውም ፥ ያማራ ፡ ሰፊነት ፡ ግዙፍ ፡ አካል ፡ በነበሩት ፡ በታላቁ ፡ ዳግማዊ ፡ ዐፄ ፡ ምንይልክ ፡ ዘመን ፥ በሐረርጌ ፤ በዐድዋና ፡ በወለጋ ፡ በኩል ፡ በግፍ ፡ ከዘለቁበት ፡ ጠላቶች ፡ ሲከላከል ፡ በለገሰው ፡ ንጹሕ ፡ መሥዋዕትነት ፡ ሲያሸበርቅ ፡ ታይቷል ። ኋላም ፥ በማይጨው ፡ ዘመቻና ፥ ይበልጡንም ፡ ባርበኝነት ፡ ተጋድሎ ፥ መላውን ፡ ዓለም ፡ ሲያስደንቅ ፡ ቈይቶ ፥ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ.ም. ፥ በመላው ፡ ዓለም ፡ ያስተጋባ ፡ ድል ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አስገኝቶ ፥ በእስያና ፡ በዖቅያንያ ፤ ባፍሪቃና ፡ ባሜሪካ ፡ የብሶች ፡ በነበሩት ፡ ቅኝ ፡ ግዛቶች ፡ ውስጥ ፡ ያነቃው ፡ የማይጨቈን ፡ ያንገዛም ፡ ባይነት ፡ መንፈስ ፡ ነውጽ ፡ አስነሥቶ ፥ ብዙ ፡ ሕዝቦች ፡ ደም ፡ ተፋሰው ፡ ሐርነት ፡ ቢወጡ ፥ ለዚህ ፡ አደገኛ ፡ ድፍረት ፡ አርኣያ ፡ የኾነችው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ነች ፡ ያሉ ፡ ኀያላን ፥ ርሷን ፡ የሚያጠፉበትን ፡ ሰፊ ፡ ዐቅድ ፡ አቁመው ፥ ላፈጸጸም ፡ አውጥተውት ፡ ኖሮ ፥ ከእንግዲህ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ዠግኖች ፡ ሊባሉ ፡ ሞያቸው ፡ የሚጠይቅላቸው ፡ አቶ ፡ አብርሃም ፡ ያየኽና ፡ አቶ ፡ ገብረ ፡ መድኅን ፡ አርኣያ ፥ "ታላቁ ፡ ሤራ" ፡ በተባለው ፡ እሪታቸው ፥ በሙሉ ፡ ዝርዝሩ ፡ ዐትመው ፡ ትተውልን ፤ ባለመታደል ፥ አንድ ፡ ባንድ ፡ ሲፈጸምብን ፡ እናያለን ።

ጽሑፉ ፡ የሚለው ፥ ባጪሩ ፥ የኢትዮጵያን ፡ አንድነት ፡ የሚያጸናውና ፡ ኀይሏን ፡ የሚያፈላው ፥ የሚያለማውና ፡ የሚያተባው ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ ("ዴሞክራሲያዊ") ፡ ሀገራዊ ፡ ባህሏ ፡ ነው ። ርሱንም ፡ የሚቀርጸው ፥ የሚያፈልቀውና ፡ የሚያወራኘው ፥ አውላሏ ፡ መኻከል ፥ እትራሮቿ ፡ ዐናት ፡ ላይ ፡ የሰፈረው ፡ ዐማራ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ርሱን ፡ በዙሪያው ፡ ከሚገኙት ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ ለይቶ ፥ ዙሪያውን ፡ በነርሱ ፡ ማስደብደቡ ፡ ያገሪቱን ፡ ጠቅላላ ፡ ኀይል ፡ በማያጠራጥር ፡ መንገድ ፡ ይደመስሳል ። ኀይሏ ፡ አንድ ፡ ጊዜ ፡ ከተደመሰሰም ፡ ኹለተኛ ፡ እንዳታንሰራራ ፥ መሟሪያ ፡ የምታስገባበትንና ፡ የንግድ ፡ ሸቀጥ ፡ በሥልጣኗ ፡ የምታመላልስበትን ፡ በር ፡ ነሥቶ ፡ ማፈን ፥ ጸጥታን ፡ መንሣት ፥ ወዘተ. ፡ ነው ።

እንግዲህ ፥ ይህ ፡ ወጥመድ ፡ ተጠምዶ ፡ መኖሩ ፡ እውን ፡ ኾኖ ፡ እየታወቀ ፥ ዐማራን ፡ ወይም ፡ መላ ፡ ኢትዮጵያን ፡ ለማዳን ፡ የሚሠራውን ፡ ኅብረት ፡ "የዐማራ" ፡ ወይም ፡ "የመላው ፡ ዐማራ ፡ ድርጅት" ፡ ብሎ ፡ መሠየም ፥ አንዱን ፡ ኢትዮጵያዊ ፡ ሕዝብ ፥ መዠመሪያ ፥ በዐማራና ፡ ኢትዮጵያ ፥ ቀጥሎም ፥ በዐማራና ፡ ሌሎች ፡ ብዙዎች ፡

ኢ ሀ ሥ አ

ለያይቶ ፥ ጠላት ፡ አመቻችቶ ፡ እዘረጋው ፡ ወጥመድ ፡ ገብቶ ፥ ፍላጎቱን ፡ ሞልቶ ፥ ኹሉንም ፡ በገዛ ፡ እጅ ፡ ዐጥቶ ፥ አጨብጭቦ ፡ መቅረት ፡ አይኾንምን ∴ ይኾናል ። ዐማራ ፡ አልተለየኹም ፡ ቢልም ፥ ስንኳን ፡ አዋላቂ ፡ ምላስና ፡ አጣቃሽ ፡ ርሳስ ፡ አሉበት ፤ እሌሉበትም ፡ ቢኾን ፥ ሌሎቹ ፡ *"ዐማራ ፡ ከድቶናል"* ፡ ብለው ፡ ሊጠረጥሩና ፡ ሌላ ፡ አቋም ፡ ሊይዙ ፡ ይገደዳሉ ።

እኔ ፡ በበኩሌ ፡ ይህን ፡ አልመክርም ። ዐማራን ፡ ወይም ፡ የኢትዮጵያን ፡ ማንኛውንም ፡ ክፍል ፥ ሰላምኽን ፡ እንድታገኝ ፡ ከሌሎች ፡ ወንድሞችኽ ፡ ተለይተኽ ፡ ተደራጅ ፡ ቢሉት ፥ ባሕርዩ ፡ ማኅበራዊ ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ብጤውን ፡ ለማግለል ፡ አይስማማም ። አንዱ ፡ ኹሉንም ፡ አንዱንም ፡ ነው ፤ መለያየት ፡ አይቻለውም ። የፋሽስት ፡ ዐረርም ፣ መርዝም ፣ እሳትም ፡ አልለያዩት ። *"የፈረሰ ፡ ማኅበርኽን ፡ ሥራ ፤ የኾንከውን ፡ ኾነኽ ፡ ማኅበራዊ ፡ ኑሮኽን ፡ አደራጅ ፥ ዐድስ"* ፡ ቢሉት ፡ ግን ፥ ያውቅበታል ። የባሕርዩ ፡ ነውና ፥ ያሳምረዋል ። ዐማራን ፡ ለኅብረት ፡ መጥሪያ ፡ ማዋሉ ፡ እንዲህ ፡ ሕዝብን ፡ የመለያየትና ፥ ኢትዮጵያውያንን ፡ (ዐማራን ፡ ደምሮ) ፡ የማጥፋት ፡ አደጋ ፡ ሲኖርበት ፥ ዐማራን ፡ (ኢትዮጵያን ፡ በመላዋ) ፡ የሚጠብቅ ፥ ድኅነትን ፡ የሚያስገኝ ፡ ለመኾኑ ፡ ያስተማምን ፡ አይመስለኝም ። የዐማራን ፡ ስም ፡ ለኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፣ ሙሉነትና ፡ ሐራነት ፡ ማዋሉ ፡ ወይም ፡ ከኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፣ ሙሉነትና ፡ ሐራነት ፡ ጋራ ፡ ማጣመሩ ፡ ግን ፥ ኹለቱንም ፡ አካብቶ ፡ የሚያድን ፡ ስለሚመስለኝ ፥ የድርጅቱን ፡ ሥያሜ ፡ በዚህ ፡ መሠረት ፡ ቢያደርጉት ፡ ይሻላል ፡ ባይ ፡ ነኝ ። ግድ ፡ ያስፈልጋል ፡ ከተባለ ፡ ግን ፥ ማኅበርተኞቹ ፡ በወግ ፡ ሞልተው ፡ ተሰብስበው ፥ *"ስም ፡ ወደ ፡ ግብሩ ፡ ይመራል"* ፡ በሚለው ፡ ሐቅ ፡ መሠረት ፥ *"የመላው ፡ ዐማራ ፡ ድርጅት"* ፡ የሚያሠኘው ፡ ሥያሜ ፡—

- መነሻ ፡ መሠረትነቱ ፥ ማለት ፥ ኅልዮነቱ ፡ መላውን ፡ ዐማራ ፡ (መላውን ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ) ፡ ሰብስቦ ፡ ያስነሣል ፡ ወይ ∴
- መገሥገሻ ፡ መንገድነቱስ ፡ መላውን ፡ ዐማራ ፡ አከታትሎ ፡ ያጕዛል ፡ ወይ ∴
- መድረሻ ፡ ግብነቱ ፡ ደግሞ ፡ መላውን ፡ ዐማራ ፡ አጠቃሎ ፡ ያደርሳል ፣ ያድናል ፡ ወይ ∴

ሲሉ ፡ መክረው ፡ ዘክረው ፥ አዎ ፡ ብለው ፡ ሲስማሙበት ፡ ይበጃል ፡ ብለው ፡ ይያዙት ፤ አለዚያ ፥ የሚበጀውን ፡ ሌላ ፡ ይለውጡ ፡ እላለኹ ።

በሰበቡ ፡ ተከታይ ፡ ልሻለት ፡ የተነሣኹ ፡ እንደማታስመስሉኝ ፡ ተስፋ ፡ በማድረግ ፥ ሕዝቡ ፡ የሚቀበለው ፥ ወይም ፡ የሕዝብ ፡ አንድያው ፡ ፍላጎት ፡ የኾነ ፡ ኅልዮ ፡ ያለው ፡ ኅብረት ፡ ግን ፥ መጨረሻውን ፡ እንደሚያሸንፍ ፡ ለማስረዳት ፥ እኔ ፡ ያለኹበትን ፥ የማውቀውን ፡ የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ፡ (ኢ.ሀ.ሥ.አ.)ን ፡ ኹኔታ ፡ ልጠቅስ ፡ እወዳለኹ ።

ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ ስሙ ፡ እንደሚናገረው ፥ ምን ፡ ጊዜም ፡ የመላው ፡ ኢትዮጵያውያን ፡ የፈቃድ ፡ አንድነት ፡ ስለ ፡ ኾነ ፥ ኅልዮው ፡ ምን ፡ ጊዜም ፡ የነዚያው ፡ ሞላው ፡ ዐባሪዎች ፡ ብሶት ፡ ነው ። ይህም ፡ በመኾኑ ፥ ባ፲፱፻፴፩ ፡ ዓ.ም. ፥ በ*"ጥንታዊት ፡ ኢትዮጵያ ፡ ማኅበር"* ፡ ሥያሜ ፥ የኢትዮጵያን ፡ ዐርበኞች ፥ *"ኢትዮጵያን ፡ ከወራሪ ፡ ፋሺስት ፡ ኢጣሊያ ፡ ነጻ ፡ ማውጣት ፡ ወይም ፡ ሞት"* ፡ በሚል ፡ ሀገራዊ ፡ ምኞታቸው ፡ አሰባስቦ ፡ ተነሥቶ ፥ አስተባብሮ ፡ ወግቶ ፥ ባንድነቱ ፡ ድል ፡ ነሥቶ ፡ አገሩን ፡ ከሞት ፡ አድኗል ።

ካ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ.ም. ፡ ሀገራዊ ፡ ድል ፡ ለጥቆ ፥ በኤርትራና ፡ ኢትዮጵያ ፡ አንድነት ፡ ማኅበር ፡ ስም ፡ የባሕር ፡ ምድርን ፡ ወይም ፡ የመረብ ፡ ምላሽን ፡ ሕዝብ ፡ *"ኢትዮጵያ ፡ ወይም ፡ ሞት"* ፡ በሚል ፡ የወል ፡ ኅልዮ ፡ አስተባብሮ ፡ አነሣሥቶ ፥

አጋግሎ ፡ አጕዞ ፥ ሞላቸው ፡ እትንገበገቡለት ፡ ግብ ፡ ኹሉንም ፡ ባንዲት ፡ ኢትዮጵያ ፡ እነጻ ፡ ኢትዮጵያዊነት ፡ በሰላም ፡ አድርሷቸዋል ።

ባ፲፱፻፷፰ ፡ ዓ.ም. ፥ ባኹኑ ፡ ሥያሜው ፡ ሲቋቋም ፥ ዐላማው ፡ በዚሁ ፡ ሥያሜው ፡ ሞልቶና ፡ ጠርቶ ፡ የተገለጸው ፥ የመሳው ፡ ኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድያው ፡ ኀልዮው ፡ ነው ፥ ማለት ፦

ሀ) መነሻው ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ የመሠየም ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ (ዴሞክራሲያዊ) ፡ ጽኑ ፡ ፍላጎቱ ፡ ነው ፤ ተነሹ ፡ ሥልጡኑ ፡ ያው ፡ መሳው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነት ፡ ነው ፤

በ) መገሥገሻው ፥ ሥልጡንሕዝባዊው ፡ ጕዳናው ፡ ነው ፤ ገሥጋሹ ፡ ያው ፡ መሳው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነት ፡ ነው ፤

ገ) መድረሻው ፥ ሀገራዊ ፡ እግዚእናውን ፡ የመቀዳጀት ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ ሠቀቀኑ ፡ ነው ፤ ደራሹ ፡ ያው ፡ ሥልጡኑ ፡ መሳው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ሕዝብ ፡ አንድነት ፡ ነው ።

ሲሰበሰብም ፥ ሲነሣና ፡ ሲገሠግሥም ፥ ሲደርስም ፥ ከሕዝባዊ ፡ አንድነቱ ፡ ተነጥሎ ፡ የሚቀር ፡ አባል ፡ ወይም ፡ ተመቅኝቶ ፡ የሚፃረር ፡ ጠላት ፡ የለበትም ፤ አይኖርበትምም ። የርሱ ፡ ጕልበት ፡ ማነስና ፡ የጠላቱ ፡ መበርታት ፡ ለጊዜው ፡ እንደፈለገው ፡ ባያራምዱትም ፥ በባሕርዩ ፡ ጕድለት ፣ ባላማው ፡ ስሕተት ፣ በጕዞውም ፡ መሰያየት ፡ የለበትምና ፥ አያደክሙትም ፤ በመጨረሻው ፥ ርሱ ፡ እንደሚያሸንፍ ፡ ያለፉት ፡ ፈተናዎች ፡ ቀድመው ፡ ይመሰክራሉ ።

ግንቦት ፡ ፲፯ ፡ ቀን ፥ ፲፱፻፹፮ ፡ ዓ.ም. ።

*ነጋ ፡ ኀይለ ፡ ሥላሴ ፡ (ሊ. ፡ ዤኔራል) ፥*

*የጊዜያዊ ፡ ፈጻሚ ፡ ምክር ፡ ሊቀ ፡ መንበር ፥*

*ኢ.ሀ.ሥ.አ. ።*